በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦገስት 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከኦገስት 21-31 እና ከሴፕቴምበር 1-10 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ - 1 -

ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባው ስፍራዎች- 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 4 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 6 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን - 8 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 8 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ በሴፕቴምበር 1-10/2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 9 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -

እ.ኤ.አ ከኦግስት 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 10 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የተስፋፋ የደመና ሽፋንና ክምችት ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም በምስራቅ፣ በመካከለኛው እና ምዕራብ ኦሮሚያ፤ በአዲስ አበባ፤ በምስራቅ እና ምዕራብ አማራ፤ በትግራይ እና አፋር ክልል፤ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፤ በጋምቤላ ክልል፤ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል እና በሲዳማ ክልል፤ ሀረር እና ድሬዳዋ እንዲሁም በሰሜን የሱማሌ ክልል አከባቢዎች ላይ ከነበረው ጠንካራ እና የተስፋፋ የደመና ክምችት ጋር ተያይዘው በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአምደወርቅ 43.7፤ በገለምሶ 95.0 እና 81.6፤ በላሬ 40.0፤ በሻዉራ 62.6፤ በአልጌ 50.0፣ 40.0፤ በላንጌ 42.3፤ በቁሉቢ 52.6 እና 49.5፤ በባህርዳር 53.4፤ በእንዋሪ 42.6፤ በፅፅቃ 46.2፤ 44.2፣ 64.4 እና 47.6፤ በአማን 56.9፤ በመተማ 73.6 እና 40.0፤ በጨፋ 41.2፤ በአይራ 43.5፤ በአርጆ 46.6 እና 44.4፤ በአሶሳ 57.0፤ በአፅቢ 64.0 እና 55.8፤ በቡሌን 51.4 እና 40.1፤ በጭፍራ 40.5፤ በፍቼ 80.0፤ በወሊሶ 59.0፤ በጅንካ 47.3፤ በሽሬ 53.7፤ በአማን 45.2፤ በገዋኔ 51.6፤ በሁንዱፎ 144.6፣ 85.2፣ 99.4 እና 137.4፤ በወላይታ ሶዶ 45.6 እና 44.6፤ በባቱ 44.8፤ በጨለንቆ 63.0፤ በኩርፋ ጨሌ 77.4፤ በግራዋ 60.0፣ በሀረር 80.0 እንዲሁም በአይሻ 88.0 ሚ.ሜ. የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት ቀናት በ74 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.0-144.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል ባህርዳር፣ አማን፣ ቡለን፣ ፍቼ፣ ገለምሶ፣ ወሊሶ፣ መተማ፣ ሻዉራ፣ ሽሬ፣ አፅቢ፣ ፅፅቃ እና ሁንዱፎ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባው ስፍራዎች

ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ አርሲ ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ የማዕከላዊ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል አዊ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ዋግህምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ ጎንደር፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኘዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን እና ኤረር ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች እንድሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ ከ180-472 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ8-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2) ፡፡ በተጨማሪም ከአፋር ክልል አውሲ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፤




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀላባ ዞን እንዲሁም ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ቡርጂ፣ ኮንሶ እና አማሮ ዞኖች ላይ ከ40-120 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-7 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ በኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ዋግህምራ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የማኦኮሞ ልዩ ዞን፣ ካማሺ፣ አሶሳ እና መተከል ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከአፋር ክልል አውሲ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ እና ፋፋን ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የየም ልዩ ዞን፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ሀላባ፣ ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ጋሞ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋ እርጥበት ነበራቸው፡፡ የነበረው እርጥበትም ለማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ እና ጤፍ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች እና ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡

በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ የጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተትና መሰንጠቅ እንዲሁም በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛትና መጥለቅለቅ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ በተለይም በሰሜን ሸዋ ዞን በኤፌራታ ግድም ወረዳ በደረሰው የመሬት መንሸራተት በተለያዩ ሰብሎችና ንብረት ላይ ጉዳት የደረሰ ሲሆን እንዲሁም በሀረር ገለምሶ ወረዳ ከነበረው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በሰብሎች እና በንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ ከተለያዩ የመስክ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአባይ፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ገናሌደዋ፣ ዋቤሸበሌ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በተለይም በላይኛው ተከዜ በጥቂት የላይኛው እና የመካከለኛው አባይ፣ ኦሞጊቤ እና ዋቤሸበሌ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም በኦሞ ጊቤ ቁጥር 1፣ የመልካ ዋከና፣ የቆቃ፣ የገናሌ ዳዋ ቁጥር 3፣ የተከዜ፣ ፊንጫ፣ ጣና፣ ከሰም እና ርብ ግደቦች የተሻለ የውሃ አቅም እንዲኖራቸው አዎንታዊ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል ከነበረው ከፍተኛ መጠን ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ በተከዜ፣ በተንዳሆ፣ በከሰም እና በርብ ግድቦች ላይ የውኃ መብዛት ጫና አስከትሏል (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በመጪዎቹ አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በተስፋፋና በተጠናከር ሁኔታ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅና እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጠንካራ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በፀሐይ ሀይል ታግዞ ከሚፈጠረው ጠንካራ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ በረዶና ነጎድጓድ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራል(ካርታ 6)፡፡ በመሆኑም ከሚኖረዉ ተደጋጋሚነት ካለዉ ከባድ መጠን ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለጎርፍ መከሰት እንዲሁም የመሬት መንሸራተት የማስከተል አቅም ስለሚኖረዉ የሚመለከታቸዉ አካላት አስፈላጊዉ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል (ካርታ 6 እና 7) ፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ከትግራይ ክልል ደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ ዋህግምራ፣ አዊ፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሃሪ፣ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ እና ካማሺ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣ አኝዋክ፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ሀላባ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ዞኖች፣ ጠምባሮ፣ ቀቤና እና ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ኮንታ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ጌድኦ አማሮ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ ከመደበኛ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ይኖራቸዋል። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፤ ከሶማሌ ክልል የሲቲ፣ ፋፈን፣ ኤረር፣ አከባቢዎች ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡




ካርታ 6 ኢ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ካርታ 7 ኢ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


## ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሴፕቴምበር የመጀመሪያዉ አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአብዛኛዉ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8) ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በፀሐይ ሀይል ታግዞ ከሚፈጠረው ጠንካራ የሆነ የደመና ክምችት ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Rainfall performance (mm) for 1-10 September 2024




ካርታ 8 እ.ኤ.አ በሴፕቴምበር 1-10/2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት የሚኖረው እርጥበት በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ልዩ ልዩ የመኸር ጊዜ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ከማሻሻሉም በተጨማሪ የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማቸት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ከመደበኛ በላይ ዝናብ በሚጠበቅባቸው እና ተደጋጋሚ የሆነ የእርጥበት ሁኔታ በሚስተዋልባቸው ቦታዎች ቅጽበታዊ ጎርፍ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ከመፈጠሩ ጋር ተያይዞ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ በሚገኙ ሰብሎች አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረው ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸው፣ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑና በውሃ መብዛት በሚጠቁ ቦታዎች አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን ውሃ ከማሳ በማስወገድ፣ የጎርፍ ውሃ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀትና በሰብሎችና በእንስሳት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የመሬት አቀማመጣቸው ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተትና መሰንጠቅ ሊኖር ስለሚችል ለመሬት መንሸራተት ከፍተኛ ስጋት ካለባቸውና ተጋላጭ ከሆኑ አካባቢዎች ማህበረሰቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም ከሰብል ጥበቃ አንፃር ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር ለፀረ ሰብል ተባይ አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ስለሚችል በየዕለቱ የማሳ ጉብኝት በማድረግ፣ አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ መሰረት በመተግበርና ጥንቃቄ በማድረግ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦግስት 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት አባይ፣ ተከዜ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ያገኛሉ። ይህም ሁኔታ የተለያዩ የመስኖም ሆነ የኃይል ማመንጫ ግድቦች በቂ የውኃ ሀብት ማከማቸት እንዲችሉ ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኦሞ ጊቤ ቁጥር 1፣ የመልካ ዋከና፣ የቆቃ፣ የገናሌ ዳዋ ቁጥር 3 እና የተከዜ ግድቦች ተጨማሪ ውኃ ለማከማቸት ያስስላል፡፡ በአንጻሩ ግን በተደጋጋሚ እየጣለ ካለው ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ ጋር ተያይዞ እንደ ፊንጫ፣ ጣና፣ ቀሰም እና ርብ ግደቦች አሁናዊ የውኃ ከፍታቸው የጨመረ በመሆኑ በመጪው አስራ አንድ ቀናት ተጨማሪ የውኃ ፍሰት ወደ ግደቦች ሊገባና ከግድቦቹ ውኃ የመያዝ አቅም በላይ ሊደርስ ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት የቅርብ ክትትል በማደረግ አስፈላጊውን አርምጃዎችን አስቀድሞ ማከናወን ያስፈልጋል። በተጨማሪም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑት የአባይ፣ ተከዜ፣ ስምጥ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሸለቆ፤ በባሮ አኮቦ፣ አዋሽ እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ቅጽበታዊ ጎርፍ እና የወንዞች ሙላት ሊከሰትና በህይወት፣ በንብረት እና በመሰረተ ልማት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ነባር የውሃ ማፋሰሻ ቦዮችን ማፅዳት፣ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማፅዳትና ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et